# ስለ ያሬድ ጥበቡ እኔም የምለው አለኝ

## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ/Ethioplan Semay)

በእኔ እና በአሲምባ ድረገጽ አዘጋጆች ጋር የከረረ ልዩነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ። ምን እያደረግህ ነው እዚህ አሲምባ ድረገጽ የምትሉ ልትኖሩ ትችሉ ይሆናል። እዚህ ልገኝ ያስገደደኝ ምክንያት የአሲምባ ድረገጽ ዋና አዘጋጅ አቶ ሰውየው በያሬድ ጥበቡ ላይ የተቸውን ትችት አስፈላጊና አስተያየት ለመስጠት ነው።ትችቱ እዚህ ድረገጽ ስለተለጠፈ፤የግድ ትችቱ በተሰጠበት ድረገጽ ላይ መተቸት ለአንባቢዎች ተከታታይ ትምህርት ለማስጨበጥ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘሁት ነው።

ግርም! (ላላ ተደርጎ ይነበብ) ይላል ትግሬ። ግሩም ነው። በ'ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ' በአህዴን/ብአዴን/ መጋበሪያ (ትግርኛ) እጀታ (አማርኛ) tool/gadget (እንግሊዝኛ) በነበረው በአቶ ያሬድ ጥበቡ ላይ የሰነዘረው ትችት ጠቃሚ እና አቶ ያሬድ በአመርቂ የአገላለጽ ዘይቤውና የተፈጥሮ ችሎታው ተጠቅሞ ሁሌም በሚገለባባጥበት አቋመ ቢስ አንዳንዴም "ግራ የሚያጋባ፤አፍራሽ..."አስተያየቱ ላይ አቶ ሰውየው አቶ ያሬድ ጥበቡን እንድናየው የሰነዘረው አጠቃላይ የሰፋ ትችት /gamut/ ማንበብ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። "ድሮ ነበር አንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ" የሚለው የአቶ ሰውየው ትችት ላማንበብ በሚከተለው ማስፈንጠሪያ ይመልከቱ http://www.assimba.org/Articles/Qedmo_Neber_Enji_MetnoMedeqos_ed.pdf

አቶ ያሬድ፤ተኮላ ሓጎስ፤መሳይ ከበደ፤ጌታቸው በጋሻው (ዶ/ዜሮ) እና የመሳሰሉ ስማቸው እዚህ ለመዘርዘር እጅግ ብዙ የሆኑብኝ የኢሳት አለቅላቂ ምሁራኖችና ከሻዕቢያው ቀዳሽ እና አወዳሽ ከሆነው ኢሳት በሚያዘጋጀው 'አስረሽ ምቺው' እስክስታ የሚወርዱ፤እጃቸው እስኪግል የሚያንጨበጭቡ፤ ፍጮታቸው የሚያቀልጡ  የድሮ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ወታደራዊ መኮንኖች ተመሳሳይነታቸው በአንድ መስመር የሚካተቱ ናቸው። ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ለተነሱ የተለያዩ ደርጅቶች 'ለጎጂ መንገድጠረጋ' አመቺ አጋሮች ('ለሳብቨርዥን') የሚሆኑ ናቸው ብየ እገልጻቸዋለሁ። በቀላሉ እባብ ጎትትው ልያመጡብን የሚችሉ ናቸው ብየ ባጭር አገላልጽ ብገልጽቻው ይሻላል።

አቶ ያሬድ በሳላ ሰው ሆኖ ግን ፈረንጆች "ሚዲዮክሪቲ" (ሄደም መጣም የማይጎዳና የማይጠቅም) የሚሉት ዓይነት ነው። በተለያዩ ወቅቶች የሚጽፋቸው ጽሑፎቹ ለሚከታተል ሰው በተለይ ጠለቅ ያለ በሳላ ሕሊና ለሌለው (ፖለቲካውን ለረዢም

ያልተከታተለ አንባቢ) አጅግ የሚመስጥ ተቺና ብረቱ የብዕር ሰው ነው። ስለሆነም እንዲህ ያሉ ምሁራን ከጥቅማቸው ይልቅ አፍራሽ ሲሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ያመዝናል።

አቶ ያሬድ ዛሬ ፡የተናገረው ነገ በተቃራኒ እራሱን ሲጻረር ታዩታላችሁ። ለምሳሌ በመለስ ዜናዊ ሕመም ውቅት እና በመስ ዜናው ዕረፍት የሰጠው አስተያየት እንዲሁም ከመለስ ዜናዊ ሕልፈት በኋላ "ከኢቲቪ ምስሎች በስተጀርባ" የሚለውን ጽሑፉን ስታነጻጽሩት እረስ በርስ የሚምታቱ ናቸው።ለምሳሌ Awramba Times - Yared Tibebu's remark on Bereket Simon's statement about Meles Zenawi | August 2012 የሚለውንም የቪዲዮ ቃለ ምልልስም ሆነ በሌላ በቅርቡ ደግሞ "አስቸኳይ መልዕክት! ይድረስ ለብአዴን አመራር" የሚለውን ጽሑፉ ጉጉል ስታደርጉ ያሬድ በግልጽ ልታውቁት ትችላላችሁ። ባንድ በኩል መለስ በመሞቱ "ኢትዮጵያ አንድ ሰው አጣች" በማለት የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ሲሰራ፤ ባንድ በኩል ደግሞ በቅርቡ ከላይ በተጠቀሰው ርዐስ የለቀቀው ጽሑፉ ውስጥ፤ የሚከተለው ብሏል።

"በጥቅምት 1968 ዘገብላ በተባለ ቦታ ቲኤል ኤፍ የተሰኘውን የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት አመራር አባላት ድርጅታዊ ውህደት እንፈፅም" ብሎ ከተሰበሰቡ በኋላ እዚያው አፍኖ በመግደል ደም ከጠጣ ጀምሮ በደም አበላ እንደተዘፈቀ የኖረ ሀይል ነው።" በማለት "በደም አበላ የተዘፈቀውን ድርጅት/ሀይል መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ ሲሞት፤ "ኢትዮጵያ ዛሬ አንድ ሰው አጣች" ብሎ የነገረን ሰውየ በቅርቡ ደግሞ 350 ዲግሪ ታጥፎ በደም አበላ የተዘፈቀ ድርጅት መሆኑን ለብዕዴኖች ያስጠነቅቃቸዋል። የትቻውን አባበሉን እንጨብጥ?

ስለ መለስ ዜናዊ መታመም ከአውራምባ ታይምስ ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ምን ይላል? ወዳጁ በረከት ስምዖንስ ከ 'ኤስ ቢሲ" ራዲዮ ያደረገው ምልልስ ምን ይላል?

በመጀመሪያ በረከት ስምዖንን እናድምጥ። በረከት የወያኔ ስርዐት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮችሐላፊ ነበር። ባንዳው መለስ ዜናዊ በ52 ቀናት (ሞቶም ሆነ ታምሞ) በመሰወሩ ምክንያት በረከት እንዲህ ይላል።

ኤስ ቢ ኤስ ራደዮ (ካሳሁን ሰቦቃ) አንዲ ይጠይቃዋል፡

ስለ አቶ መለስ ሁኔታ ሊነግሩን ይችላሉ?

በረከት ፤

አስፈላጊውን ዕረፈት እንዲወስዱ የተመከሩበት ሁኔታ ስለነበር ይህንን መነሻ በማድረግ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ዕረፍት ላይ ነው የቆዩት።ዕረፍታቸውን አጠናቅቀው በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚመለሱ ተስፋ እናደርጋለን። ጤንንታቸውም በጥሩ ሁኔታ ናቸው ያሉት።

ኤስቢኤስ ራዲዮ፤

ሁሌም እንደሚያደርጉት በዘመን መለወጫ ወቅት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ለሕዝቡ ለማስተላለፍ በወቅቱ ይገኛሉ ብለው በዕርግጠኛነት መናገር ይችላሉ?

በረከት ፤

አዎ እጅግ፤ እጅግ በእርግጠኛነት ሆኜ! ከዚያ በፊት እንደዛ ይሆናል፤ በጣም በጥሩ ሁኔታ ናቸው ያሉት ብየ ለመናገር እችላለሁ።

ያሬድ ጥበቡ ደግሞ ለአውራምባ ታይምስ የሰጠው የበረከት ድጋፍ እንዲህ ይላል።

'በረከት ካሁን በፊት ስለ መለስ ተጠይቆ ሲመልስ ሁለት ወይንም ሦስት ጊዜ ይመስልኛል። ይኼኛው ካሁን በፊት ከሰጣቸው ይበልጥ ተአማኒነት ያለሁ ሆኖ ተሰምቶኛል።በረከት ለብዙ አመታት የማወቀው ሰው ነው፡ እና የተናገረበትን ደምፀቱ፤በመስመሮች መሃል ላይ ለመናበብ መከሬአለሁ፡በዛው ሁሉ የገመትኩት ነገር፤ እውነቱን የሚናገር ሰው ነው ያዳመጥኩት፡' ይላል አንጋፋው ፓለቲከኛ ያሬድ ጥበቡ።

ይህ ብቻ አይደለም። ያሬድ መለስ ዜናዊ "ሞቷል" ከተባለ በኋላም ስለ መለስ ዜናዊ ሞት የተሰማውን ስሜት እንዲገልጽ ተጠይቆ ሲመልስ እንዲህ ይላል።

"ዛሬ ኢትዮጵያ አንድ ሰው አጣች!" ነው ያለው። እሱ ብቻ አይደለም ልደቱ አያሌውም፤ በቀብሩ ባለመገኘቱ (እንግሊዝ አገር ለትምህርት/ስልጠና (?!) ስለነበር) እጅግ አዝኖ "ዛሬ ኢትዮጵያ አንድ ሰው አጣች!" ብሎናል። እነኚህ ናቸው "አንጋፋ ፖለቲከኞቻችን" ተብለው የሚጠሩት። መለስ በማጣትዋ ኢትዮጵያ እንዴት አንድ ሰው አጣች እንደተባለላት ለኔ እጅግ አስገራሚ ከመሆኑ በላይ አውጥቼ አውርጄ እንዲህ ያሉ በሳላ ሰዎች እንዲህ ባለ አጅግ አሳፋሪና ደካማ ስሜትና ደምደማ ሊደርሱ እንደቻሉ መልስ ፈልጌ ላገኝለት አልቻልኩም።

ያሬድ ጥበቡ እኔን እና የመሳሰሉት የጸረ ኢትዮጵያው የባንዳው መለስ ዜናዊ ሞት በኢትዮጵያ አምላክ ትዕዛዝ እና በሕዝብ ዕንባ ምክንያት ከዚህ ዓለም "ተሎ በመቀጨቱ' ምክንያት ደስታችንን የገለጽን እውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያዊያንን "ከፋዎች እና

የፖለቲካ አላዋቂዎች” ሲል ለድሮ  የበረሃ ጓዱ የሚዲያ እንባውን አፍስሶ በሚገርም ዘለፋ ዘልፎናል። ሰፊውን ዘላፊውን ለማድመጥ የሰጠሁዋችሁን “ሊንክ” አድምጡ።

ያሬድ እኛን ከኢትዮጵያ መንፈስ ውጭ የሆኑ ተጻራሪዎች፤ኩፉዎች እና የፖለቲካ ደናቁርት፤... ሲል ኮንኖናል። የኢትዮጵያ መንፈስ ምን ማለት ነው? ሕዝብን ለሕዝብ ያጋደለ፤እናቶቻችንን እያስጮኸ እምባ እያፈሰሱ የረዳት ያለህ ልጆቻችን ገደለብን፤ድረሱልን እያሉ እሪ እንዲሉ ያስደረገ፤ አዛውንቶችን እምባ እንዲያቀርሩ ያስደረገ፤ አዛውንት ሚስትቶቻቸውን አንዲያጡ ወደ ገደል እንዲጨመሩ ወታደሮቹ ወንጀል ሲፈጽሙ ችል ብሎ የተመለከተ፤ የአማራ እናቶች እና አራስ/እመጫቶች ከተጋደሙበት መደብ እየተጎተቱ ደማቸው እያንጠበጠቡ እንዲባረሩ ከጉራ ፈርዳ፤ ከኦሮሞ ገጠሮችና ከተማዎች እየተደበደቡ ሲባረሩ፤ “እሰየው፤ ጫካ ሲመነጥሩ የነበሩ ሕግ አልባ ፤ሕግ የጣሱ እና “ጉራ ፈርዳ የአማራ መንደር እስኪመስል ድረስ የሰፈሩና” ናቸው ብሎ በፓርላማ ላይ ስሜቱን የገለጸ ፋሺስት ግለሰብ”፤ በግፍ  አብየተ መወቅደሳትን/ መስጊዶች ሲቃጠሉ በቸልተኛነት የተመለከተ፤ሃይማኖትን ያራከሰ፤ ሃይማኖትን ወደ ፖለቲካ ዕምነት ያስለወጠ፤ እስላም እና ክርስትያን ያናከሰ፤ ኦርቶዶክስንና አማራን አከርካሪውን መሰበር አለበት ብሎ በተግባር ያስፈጸመ፤ የሕዝብ መላያ የሆነቺውን ሰንደቃላማን የዘለፈ፤ያንቋሸሸ፤ ሕጻናት እና ወጣቶችን በጥይት አናታቸውን ላይ ኢላማ የሚጫወት፤ አስሮ አዋርዶ፤ በወንዶች ላይ ግብረሰዶም እና በሴት ፖለቲከኞቻችንም ላይ እሰር ቤት እያሉ የጾታ አመጽ የሚያካሂድ . ኢትዮጵያን በጎሳና በቋንቋ እንድትሸነሸን ያደረገ፤ እጅግ አረመኔ የሆነ የፋሺስት ቡድን/ድርጅት/ መሪ ቢሞት ወይንም ድርጅቱ ቢፈራርስ ደስታችሁን አትግለጹ የሚሉ ምሁራኖች አሰዛኝና አሳፊሪዎች ናቸው።

ይህ ግፍ ያስፈጸሙና የፈጸሙ ግለሰቦች በፈጠሪ ትዕዛዝ በሞት ሲቀጡ ደስታችሁን አትግለጹ የሚል ወይንም አንድ ጋጠ ወጥ ወንጀለኛ ፤ እናቱን፤አባቱን፤ባለቤትዋን ፤ባለቤቱን ፤ወንድሙን፤ ወንድሟን እህቱን፤እህቷን የገደለና መንደሩን ሁሉ እሳት ያጋየ መንደር ሁሉ በሽብር የናጠ ሽፍታ/ወንጀለኛ ግለሰብ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት፤ ቤተሰቦች ‘ደስታችሁን/ደስታሺን’ በዕልልታ አትግለጹ” የሚል ኢትዮጵያዊ ባሕል/መንፈስ ካለ አቶ ያሬድ ሊጠቁመን ይገባዋል።

በፋሲካ ዋዜማ ቤተክርስትያን ውስጥ “ኮነ ፍስሃ ወሰላም” ከመባሉ በፊት ሰይጣንን እና ክርስቶስን የገደሉትን ለመግደል አይደለም ወይ ጸሎተኛ ሁሉ ተሰብስቦ ድንጋይ በመያዝ አይደለም ወይ መሬትን የሚቀጠቅጠው? አይደለም እንዴ?

ከዚያስ ደስታውን ለመገግለጽ አይደለም እንዴ ጸሎተኛ ሻማ አብርቶ በዕልልታ ደስታውን የሚገልጽ? አረመኔውና ሰይጣናዊው መለስ ዜናዊ 'እንኳን ቀዘፈው' ብለው የተደሰቱ እናቶች እንዴት ኩፋዎችና የፖለቲካ ደናቁርት ይባላሉ? በባህላችን እየተባለ የሚደሰኮር ነገር ምነ ድ ነው? ፋሲካ የምናየው ዕልልታ ሰይጣን ሲደበደብ ሲሞት በደስታና ዕልልታ እየታጀበ ነው። ኢትዮጵያዊ መንፈስና ባሕል ምን ማለት ነው?

አቶ መለስ የተፈረደበት በሕዝብ ተከስሶ፤ተወንጅሎ ወደ ፈጠራ ቀርቦ ጉዳዩ ፈጠሪ አይቶ በሞት እንዲቀጣ አድርጓል። አቶ ያሬድ በወንጀለኛው ሰውየ አዝኖ "አንድ ሰው አጣን" ማለት መብቱ ነው። እኛ ግን ድፍን አገር ያስለቀሰ ወንጀኛ በሞት ተቀጥቶ ከላያችን ላይ መውረዱ እና ለዚህ አሁን ለምናየው ለውጥ በር መከፈቱ ደስታችን መግለጻችን ትክክለኞች ነበርን ። ስለ አረመኔ ሰው አዝኖ እኛን 'የፖለቲካ ደናቁርት' ብሎ እኛን መዝለፉ ደንቆሮ ማን መሆኑን፤ ለረዢም ጊዜ የተጓዝንበት ማሕደራችን የሚፈርደን ይመስለኛል።

አቶ ያሬድም ሆነ መሰል የአረመኔ ሰው አዛኞችና አላዛኞች 'እንደ ኢትዮጵያዊያን የሚሰማን ስሜት" ለአረመኔ ሰው እና አገርን ላፈረሰ ግለሰብ አዛኝ አንጀት የለንም።እራሴን ልወክልና "የለኝም!"።ለኔ አገሬን እና ቤተሰቦቼን ላለማየት አግዶ አገሬን "እንደ የግል ንብረቱ አድርጎ" በወረበሎች ጠመንጃና ሰላዮች የሚያስቀመኝ እና ያገደኝ አረመኔ ሰው፤ ያሬድ ጥበቡ 'ኢትዮጵያዊ መንፈስ የምትለው "እኔ ጋር አታገኘውም"።

ክሳችን ወደ ፈጣሪ አቅርበን ውሳኔ አግኝተናል! ፍርዱ የሰጠው ፈጣሪ ነው! ወደ ፈጠራያችን ክስ አቅርብን አብየት ስንል ቆይተን ትንሽ ቢዘገይም ቅጽበታዊ ፍረድ ተላልፎ ከአቤቱታው ውጭ የነበራችሁ፤ አቤቱታችንን የተጻረራችሁ እነ ያሬድ እና እነ ልደቱ፤ ፍርድ አግኘተናልና ምን ትሆኑ!

የአማራ ሕዝብና አሮሞ ገበሬዎችና ህጻናት/ እንዲሁም ሌሎች ወገኖቻችን ላይ ጥይት እየተተኮሰባቸው ከቤት እንዳይወጡ ታግደው በጭለማ እና በረሃብ ሲሰቃዩ ትግራይ መቀሌ ላይ "የአሸንዳ ከበሮ" ሲነረት፤ ሽቶ እና ቀጤማ ተነስንሶ ዕልልታ ሲቀልጥ ማየት ተገቢ ስላልሆነ፤ ይህንን አናካሽ ሴራ የጎነጎኑ ግለሰዎች ላይ ፈጣሪ ታምራዊ ፍርዱ እንዲያስተላልፍ "በመለስ ዜናዊ ላይ ሞትን ያስተላለፈውን ብይን' በተቀሩ አረመኔ መሪዎችም ላይ ውሳኔውን እንዲሰጠን ሁሉም ለማይሳነው ወደኢትዮጵያ አምላክ አቤቱታችንን በዝርዝ አቅርበናል። ፍርዱም በቅርቡ እንሰማለን። ያኔ እነ ያሬድ ጥበቡም ሆናችሁ እነ ልደቱ አያሌው እንዲሁም እነ ታማኝ በየነ፤ "የመለስ ሞት ሲነገራችሁ" 'ክው' ብላችሁ በሃዘን ስሜት ልባችሁ እንደተነካ ሁሉ እንደለመዳችሁበት ስሜታችሁ

በፈጣሪ ፍርድ ሸንጎ “ስብሓት ነጋም ሆነ ሌሎች አረመኔዎች” የሞት ፍርድ ሲተላለፍባቸው፤ ከው ብላችሁ የደነዘዛችሁበት የሃዘን ስሜታችሁ የፈጣሪን ውሳኔ በመቃወም እንደገና እንደምትግልጹልን ተስፋ አለን። እናንተም በሃዘን እኛም በደስታ እንገመገማለን። አቶ ያሬድ ጥበቡ በቀርቡ በገለጸው ጽሑፉ ላይ “ዳያስፖራ ውስጥ በምንኖረው ኢትዮጵያውያን መሃል የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሕይወትና ሞት እንዳከራከረን ኖሮአል።” እንዳለው በፈጣሪ ችሎት ላይ ተከስሰው ፍረዳቸውን በመጠባበቅ ላይ ያሉ ወያኔዎችም በፈጣሪ ችሎት ላይ የሞት ቅጣት ሲበየንባቸውም፤ በነሱ ሕይትና ሞት ላይም በናንተ እና በኛ ላይ ክርክራችን ይቀየጥላል። እስከዘው ሰላም ለሁላችን ይሁን

ጌታቸው ረዳ (የኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ Ethiopian Semay)
getachre@aol.com